# ወያኔ በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ላይ የሞት ፍርድ?!

## አመድ በዱቄት ይስቃል

ከአያልነሽ

ፈጣጣው ወያኔ ፈጣጣ ነውና በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ላይ በሌለበት የሞት ፍርድ ፈረድኩበት ብሎናል። ወያኔ ለሚያደርገው ድርጊት ሁሉ ልጠይቀው ብሎ የሚነሳ ሰው ካለ ጠያቂው ሰው የሚታዘንለት እንጅ የሚታዘንበት ላይሆን ይችላል። በእኔ እይታ አንድ ሰው ጥያቄ ሲጠይቅ ለሚጠይቀው ጥያቄ ቢያንስ የተሟላ መልስ ባያገኝም እንኳ፣ ተጠያቂው ከጠያቂው የተሻለ ነው ብሎ በመገመት ነው ጥያቄውን ለመወርወር የሚሞክረው። ለዚህም ነው ከመነሻዬ ወያኔ ለሚያደርገው ድርጊት ሁሉ ”ለምን ይሄን ያደርጋል?” ብሎ የሚጠይቅ ካለ ወተት ለምን ነጭ ሆነ ብሎ እንደመጠይቅ ያህል ነው።

ይሉኝታ ቢሱ ወያኔ በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ላይ የሞት ፍርድ ሲፈርድ ማጠየቂያ አድርጎ ድራማ የሠራበትና የሚሰራበት፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አንድ ትውልድን የመተረው ”ቀይ ሽብር” ተብሎ የታወቀውን እልቂት ነው። በዚህ የሽብር ሂደት ወያኔም በትግራይ ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ቀይ ሽብር ተብሎ የሚጠራው ያ አሰቃቂ ፍጅት በመላው ኢትዮጵያ የተካሄደ ነበርና በትግራይ ውስጥም ይህ ሽብር ለወያኔ እንደ መና የወረደለት ስለነበር በሚችለው ሁሉ ሽብሩን አብሮ አካሂዷል።

ወያኔ ይህንን ሽብር ከደርግ ጋር ሲያካሂድ ከጅምሩ የወያኔን የጠባብነት ዓላማ የተፃረሩትን ኢትዮጵያዊ የሆኑ የትግራይ ልጆችን ”የኢሕአፓ አባሎች ናቸው” በማለት ለደርግ የተሳሳተ መረጃ በማቀበል አስጨፍጭፏል። ውቅሮ፣ አዲግራት፣ አክሱም፣ ተምቤን፣ አድዋና መቀሌ በዚህ ሽብር ያለፉ ናቸውና ይህ እውነታና መረጃ በእያንዳንዱ ቤት እጅ የሚገኝና ማህተምም ስለሆነ ጊዜን የሚጠብቅ ነው። በወቅቱ ወያኔ ይህንን ሽብር የስጠታ ያህል ነበር የቆጠረው።

በጎንደርና በጎጃም ደግሞ እነ ገ/ሕይወት የወያኔ ሰርጎ ገቦች ሆነው ደርግ ውስጥ በመግባት ደርግ ከፍተኛ ቦታና ሥልጣን ሰጥቷቸው የጎንደርንና የጎጃምን ሕዝብ ሲጨፈጭፉ ኖረው ገ/ሕይወት የተባለው የደርግ ቀንደኛ ሰው በአውሮፕላን አደጋ መሞቱ አይዘነጋም። ገ/ሕይወት ያን ሁሉ ጭፍጨፋ በሚያደርግበት ወቅት ደርግ በሽብር ደም ሰክሮ ነበርና የገ/ሕይወትን የወያኔ ሰርጎ ገብ መሆኑን ያወቀው ሕይወቱ ከአለፈ በኋላ ነበር። ወያኔ በጫካ ”የትግራይ ነፃ አውጭ” ነኝ ብሎ የነፃ አውጭ ሽብርተኛ የነበረ፣ አሁን ደግሞ ”መንግሥት ነኝ” ብሎ በመላ ኢትዮጵያ መንግሥታዊ ሽብር እያካሄደ የሚገኝ ቡድን፣ መንግሥቱ ኃ/ማርያምን በሌለበት በሞት ቀጣሁ ካለ፣ ዛሬ አገርን እየገደለና እየሸጠ ላለ ወንበዴስ ብይኑ ምን ይሆን?

ወገኛ! ወያኔ ብሎ ብይን ሰጭ! አመድ በዱቄት ይስቃል አሉ!

AP






| | ዘመነ ደርግ | ዘመነ ኢህአዴግ |
|---|---|---|
| 1. | አርማው -ጋሻና ጦር | ጠብመንጃ |
| 2. | የሸንገላ ቃሉ - አንድነት | ዴሞክራሲ |
| 3. | የኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት በጀግኖችች ልጆቿ ተከብሮ ይኖራል | ልዩነቶቻችንን መሰረት በማድረግ በህዝቦቿ መፈቃቀድ አዲሲቷ ኢትዮጵያ ትመሰረታለች |
| 4. | ታፍራና ተከብራ የኖረችው ውድ እናት ሀገርህ ጠሏቶቿ ሊደፍሯት ተነስተዋል | ወያኔ ትምክህተኞችና ነፍጠኞች ዛሬም ጦርነት ሊያውጁብህ ይፎፎጣሉ |
| 5. | ኢሠፓ የአዲሱ ሥርዓት መሪና አደራጅ ኃይል ነው | የኢህአዴግ መስመር ብቸኛ የሰላምና የዴሞክራሲ መንገድ ነው |

| | | |
|---|---|---|
| 6. | ሻዕቢያና ወያኔ አባትና ልጅ ናቸው | ደርግና ኢሠፓ አንድም ሁለትም ናቸው |
| 7. | በአንድ እጇ መስቀሌን በሌላው እጇ ጠብመንጃ ይዤ ለኢትዮጵያ አንድነት እታገላለሁ | በተ ክርስቲያናችን ለሰላምና ለዴሞክራሲ ስትል ከሽግግር መንግሥቱ ጎን ትቆማለች |
| 8. | በትግራይ በተካሄደው ውጊያ ያለቀው የወንበዴ መንጋ ብቻ ነው | በታህሳሱ 26ቱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሕገ-ወጥ ሰልፍ የሞተው ኢሰፓ የነበረ ብቻ ነው |
| 9. | ለአሶሳው ኢሰብዓዊ ጭፍጨፋ ተጠያቂው ሻዕቢያኔ ወያኔ ናቸው | ለሃውዜኑ አረመኔያዊ ተጠያቂው የደርግ ፋሽስት ነው |

(የሰንጠረዡ ምንጭ፡ አዕምሮ መጽሔት፣ ቅጽ.1 ቁ.8/ጳጉሜ 1985)

**የህዝብ ድምፅ ይከበር!**
**የታሰሩ የፖለቲካ እሥረኞች ይፈቱ!**
**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!**
በቸር ይግጠመን!
ጁን 6/2008